# በጫት ላኪ ማህበራት እና በግል ጫት ላኪዎች አማካኝነት ወደ ጅቡቲ የሚላከውን የጫት መጠን ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ

1. **አውጪው ባለሥልጣን**

የንግድና ኢንዱስትሪ ሚ/ር በአዋጅ ቁጥር 67/1989 አንቀጽ 41 መሠረት ያወጣውን ጊዜያዊ መመሪያ ቁጥር 4/1993 በማሻሻል ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

2. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "በጫት ማህበራትና በግል ጫት ላኪዎች አማካኝነት ወደ ጅቡቲ የሚላከውን የጫት መጠን ለመወሰን የወጣ የንግድና ኢንዱትስትሪ ሚኒስቴር መመሪያ ቁጥር 538/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

3. **ዓላማ**

የዚህ መመሪያ ዓላማ የጅቡቲ መንግሥት ከኢትየጵያ ወደ ጅቡቲ በየቀኑ እንዲገባ የወሰነውን የጫት መጠን በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ በጫት ላኪነት ለተሰማሩ የንግድ ማህበራትና ግለሰብ ነጋዴዎች ለመደልደልና ወደፊትም በዚሁ ሥራ የሚሰማሩ ሌሎች ማህበራትና ግለሰብ ነጋዴዎች ወደ ጅቡቲ ጫት ለመላክ ሲያሚሉ የሚገባቸውን ሁኔታ ለመወሰን ነው፡፡

4. **ትርጓሜ**

በዚህ መመሪያ፤

4.1 "ሚኒስቴር" ማለት የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነው፡፡

4.2 "የጫት ላኪ ማህበር" ማለት በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ተቋቁሞና ተገቢውን የንግድ ሥራ ፈቃድ አውጥቶ ከኢትዮጵያ ወደ ጅቡቲ ጫት ለመላክ የሚያስችለው የፀና የሽያጭ ውል ያለው የንግድ ማህበር ነው፡፡

4.3 "ሶጂክ" ማለት ከኢትዮጵያ ወደ ጅቡቲ ጫት ከሚልኩ ማኅበራት ላይ ጫት የሚቀበል በጅቡቲ የሚገኝ ድርጅት ነው፡፡

4.4 "የግል ጫት ላኪዎች" ማለት የፀና የንግድ ፈቃድ ኖሯቸው ከኢትዮጵያ ወደ ጅቡቲ ጫት የሚልኩ ግለሰብ ነጋዴዎች ናቸው፡፡

4.5 "የጫት ኮታ" ማለት በማህበራት እና በግል ጫት ላኪዎች አማካኝነት በየቀኑ ወደ ጅቡቲ እንዲላክ በዚህ መመሪያ መሠረት የሚወሰነው የጫት መጠን ነው፡፡

4.6 "የተጣራ ክብደት" ማለት ጫት ላኪዎች የጫቱን ጥራት ለመጠበቅ ለመጠቅለያ የሚጠቀሙበት ከጠቅላላ ክብደቱ 5% /አምስት በመቶ/ ተቀናሽ ሆኖ ቀሪው የጫት ክብደት ነው፡፡

## 5. በማህበራት እና በግል ላኪዎች ለሶጂክ የሚላከውን የጫት መጠን ስለመወሰን

5.1 ሶጂክ በቀን 5200 ኪ.ግ 2ኛ ደረጃ ጫት ከማህበራት እና 500 ኪ.ግ 1ኛ ደረጃ ጫት ከግል ላኪዎች መግዛት እንደተፈቀደለት የጅቡቲ መንግሥት መወሰኑን መሠረት በማድረግ፣

| | ያልተጣራ ክብደት /በኪ.ግ/ | የተጣራ ክብደት /በኪ.ግ/ |
|---|---|---|
| ▪ የኢትዮጵያ የጫትና የእርሻ ውጤቶች ላኪ አ.ማ | 895 | 850 |
| ▪ ቢፍቱ ዲንሾ ኃ/የተ/የግ/ማ | 2179 | 2070 |
| ▪ በርዋቆ የጫት ላኪዎች አ.ማ | 1137 | 1080 |
| ▪ ኩልምዬ ትሬዲንግ አ.ማ | 716 | 680 |
| ▪ ሁምበና ጨርጨር አ.ማ | 547 | 520 |
| ድምር | 5474 | 5200 |

ያላነሰ 2ኛ ደረጃ ጫት በየቀኑ እንዲልኩ እና

- የግል ላኪዎች ደግሞ 500 ኪ.ግ 1ኛ ደረጃ ጫት በየቀኑ ለሶጂክ እንዲልኩ ተወስኗል፡፡

5.2 በቁጥር 5.1 የተጠቀሱት ማህበራት በኮታ ድልድሉ መሠረት ከሶጂክ ጋር ሕጋዊ የፀና ውል መፈራረም አለባቸው፡፡

5.3 አዳዲስ ጫት ላኪ ማህበራት ተደራጅተው ሲቀርቡ ጫት ለመላክ የሚችሉት በጅቡቲ መንግሥት ለሶጂክ ከተደለደለው የ5200 ኪ.ግ በቀን ኮታ በላይ ወደ

ጅቡቲ እንዲገባ መፈቀዱ በተጨባጭ መረጃ ሲረጋገጥና ከጫቱ ተቀባይም ጋር የተፈረመ ሕጋዊ ውል ሲቀርብ ነው፡፡

5.4 በተራ ቁጥር 5.3 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በዚህ መመሪያ የተፈቀደውን ኮታ እንደገና ሊደለድል ይችላል፡፡

5.5 ማህበራት በልዩ ልዩ ምክንያት በኮታው መሠረት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ጫት ማቅረብ የማይችሉ ሲሆን ሁኔታውን ከ48 ሰዓት በፊት ለድሬዳዋ ውጭ ንግድ ጽ/ቤት፣ ለምሥራቅ ቀጠና ጉምሩክ ጽ/ቤት እና ለተቀባዩ ለሶጂክ ተወካይ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፡፡

5.6 በተራ ቁጥር 5.5 የተጠቀሰው ሁኔታ ሲከሰት የድሬዳዋ ውጭ ንግድ ጽ/ቤት ለተቀሩት ማህበራት ጥያቄ በማቅረብ በሚሰጠው መልስ ቅደም ተከተል መሠረት ሳይቀርብ የቀረውን የጫት መጠን ሲያቀርብ የሚችል ሌላ ማህበር ለሶጂክ እንዲቀርብ በማድረግ ለምስራቅ ቀጠና ጉምሩክ ጽ/ቤት ያሳውቃል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፡፡

5.7 በኮታው መሠረት መላክ የማይችል ማህበር በጊዜው ባለማሳወቁ ምክንያት ተተኪ ጫት ማቅረብ ካልተቻለም በሌሎች ማህበራት የቀረበው ጫት ብቻ እንዲላክ ይደረጋል፡፡

5.8 የምስራቅ ቀጣና ጉምሩክ ጫት ላኪ ማህበራት በተራ ቁጥር 5.1 መሠረት የተመደበላቸውን ኮታ ተገቢውን የባንክ ፈቃድ እያቀረቡ መላካቸውን፣ በተራ ቁጥር 5.5 መሠረት ከ48 ሰዓት በፊት ያላሳወቁትንና ወይም በኮታቸው መሠረት ሳይልኩ የቀሩትን እየተከታተለ በየጊዜው ለውጭ ንግድ ጽ/ቤት ያሳውቃል፡፡

5.9 በተራ ቁጥር 5.5 በተጠቀሰው መሠረት ጫቱን ማቅረብ እንደማይችል ከ48 ሰዓት በፊት ያላሳወቀ ማህበር የድሬዳዋ ውጭ ንግድ ጽ/ቤት ለመጀመሪያና ለሁለተኛ ጊዜ ጥፋት የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፣ ለሦስተኛ ጊዜ ከደገመ ግን ማህበሩን ለ1 ወር ጫት ከመላክ በማገድ ይኸው ተግባራዊ እንዲደረግ ለምስራቅ ቀጣና ጉምሩክ ጽ/ቤት ይሳውቃል፡፡

5.10 በዚህ መመሪያ ከተመለከተው ውጭ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ካልተፈቀደ በስተቀር የጫት ኮታን መደልደል አይቻልም፡፡

## 6. ከማህበራት እና ከግል ላኪዎች ለሶጂክ ከሚላከው ውጭ በግል ጫት ላኪዎች የሚላከውን የጫት መጠን ስለመወሰን፣

6.1 ማንኛውም የፀና የውጭ ንግድ ፈቃድ ያለው የግል ጫት ላኪ በጅቡቲ መንግሥት የተፈቀደለትና አስፈላጊውን የቅድሚያ ክፍያ በስሙ ያስተላለፈለት የግል ጫት ላኪ ተቀባይ እስካገኘ ድረስ ለተቀባዩ በተፈቀደለት ዕለታዊ ኮታ መጠን አንደኛ ደረጃ ጫት መላክ ይችላል፡፡ በአሁኑ ወቅት በጅቡቲ መንግሥት የተፈቀደላቸው የግል ጫት ተቀባዮች ዝርዝር ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ የተደረገ ሲሆን በጅቡቲ መንግሥት የሚደረግ ለውጥ ሲኖር በወቅቱ ይገለጻል፡፡

6.2 ተለዋጭ መመሪያ እስከሚሰጥ ድረስ በአጠቃላይ በግል ጫት ላኪዎች በየቀኑ የሚላከው አንደኛ ደረጃ የጫት መጠን /ከሶጂክ የሚቀርበውን ሣይጨምር/ ያልተጣራ ክብደት 5894.7 ኪ.ግ የተጣራ ከ5600 ኪ.ግ ያላነሰ ይሆናል፡፡

## 7. መመሪያውን የሚያስፈጽሙ አካላት

በጫት አላላክ ሥራ ላይ ቀደም ሲል በተለያዩ መ/ቤቶች ሲከናወኑ የነበሩ ተግባራት ይህን መመሪያ እስካልተጻረሩ ድረስ የሚቀጥሉ ሆነው የሚከተሉት ተግባራት ታክለዋል፡፡

### 7.1 የድሬዳዋ ውጭ ንግድ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

7.1.1 ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ሌሎች መ/ቤቶች በማስተባበር የዚህን መመሪያ አፈጻጸም በቅርብ ይከታተላል፡፡

7.1.2 በድሬዳዋ ኤርፖርት በኩል በማህበራትም ሆነ በግል ወደ ጅቡቲ የተላከውን የጫት መጠን መረጃ ከምሥራቅ ቀጣና ጉምሩክ ጽ/ቤት በየሳምንቱ ይሰበስባል፡፡

7.1.3 አዳዲስ የጫት ላኪ ማህበራት ወደ ጅቡቲ ጫት ለመላክ እንዲፈቀድላቸው ሲጠይቁ በዚህ መመሪያ በተራ ቁጥር 5.3 ውስጥ የተመለከቱት ሁኔታዎች ማሟላታቸውን እያረጋገጠ ጥያቄያቸው ተቀባይነት ያለው ሆኖ ሲያገኘው ለሚኒስቴር መ/ቤቱ አቅርቦ ሲፈቀድ አግባብ ላላቸው መ/ቤቶች ሁሉ መፈቀዱን

በደብዳቤ ያሳውቃል፡፡ ጥያቄያቸው ተቀባይነት የሌለው ሆኖ ካገኘው ደግሞ ምክንያቱን በመግለጽ ለጠያቂዎቹ በጽሁፍ መልስ ይሰጣል፡፡

7.1.4 ሶጂክ ከማህበራት የሚገዛውን መጠን ሲቀንስም ሆነ ሲጨምር ከ48 ሰዓት በፊት ለውጭ ንግድ ጽ/ቤት ያሳውቃል፣ ጽ/ቤቱም በዚህ መመሪያ ለእያንዳንዱ ማህበር የተመደበውን ኮታ መሠረት በማድረግ ይደለድላል፤ለሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶችም ያሳውቃል፡፡

7.1.5 የጅቡቲ የግል ጫት ተቀባዮች ዝርዝር በተራ ቁጥር 6.1 መሠረት ለውጥ ሲኖረው ለሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች ያሳውቃል፡፡

## 7.2 <u>የምሥራቅ ቀጣና ጉምሩክ ጽ/ቤት</u>

7.2.1 በዚህ መመሪያ ለማህበራትም ሆነ ለግል የተደለደለውን ኮታ ተግባራዊነት ያረጋግጣል፡፡

7.2.2 በየዕለቱ ለጫት ላኪዎች የማስጫኛ ሰነድ /ዲክላራሲዮን/ ይሰጣል፡፡

7.2.3 በማህበራትና በግል የጫት ላኪዎች የተላከውን የጫት መጠን መረጃ እንዲሁም ችግሮች ካሉ መግለጫ በማያያዝ ለድሬዳዋ ውጭ ንግድ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ያስተላልፋል፡፡

## 7.3 <u>ሶጂክ ኩባንያ</u>

7.3.1 በሮመዳን የጾም ወራት ወቅት የጫት ፍላጎት ስለሚቀንስና በሌላ በኩል ደግሞ በበዓላት ጊዜ የጫት ፍላጎት ስለሚጨምር ሶጂክ ከማህበራቱ የሚፈለገውን አጠቃላይ የጫት መጠን ለድሬዳዋ ውጭ ንግድ ጽ/ቤት ከ48 ሰዓት በፊት ያሳውቃል፡፡ ጽ/ቤቱም ከሶጂክ የደረሰውን ለማህበራትና ለምሥራቅ ቀጣና ጉምሩክ ያሳውቃል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፡፡

7.3.2 የሶጂክ ኩባንያ ድሬዳዋ ላይ ለተቀበለው ጫት ደረሰኝ "Goods Receipt" ርክክቡ እንደተፈጸመ ወዲያውኑ ለላኪው መስጠት አለበት፡፡

7.3.3 ሶጂክ ጫቱን ወደ ጂቡቲ ለማጓጓዝ የሚያስፈልገውን አውሮኘላን የማቅረብ ኃላፊነት አለበት፡፡ የጭነት አውሮኘላን የማይኖር ከሆነ ይህንኑ ከ24 ሰዓት በፊት ለላኪ ማህበራት ማሳወቅ አለበት

7.4 ኮታ የተደለደለላቸው ላኪ ማህበራት

7.4.1 ከተቀባዩ ሶሺክ ጋር የጸና የሽያጭ ውል መፈራረም አለባቸው።

7.4.2 በውላቸው መሠረት ደረጃውን የጠበቀ ጫት ለተቀባዩ ማቅረብ አለባቸው።

7.4.3 አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን ለባንኮች በማቅረብ ሂሣባቸውን በየ15 ቀኑ ማወራረድ አለባቸው። አንደኛ እና ሁለተኛ ጊዜ ሂሣቡን ለማያወራርድ ማህበር ድሬዳዋ በሚገኘው የብሔራዊ ባንክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በኩል የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ እንዲሰጠው ይደረጋል። ለሦስተኛ ጊዜ ከደገመ የባንክ ፈቃድ እንዳይሰጠው በማድረግ ሁኔታውን ለውጭ ንግድ ቅ/ጽ/ቤት ያሳውቃል።

8. መመሪያውን ባለማክበር ስለሚወሰድ እርምጃ

ማንኛውም ማህበር ወይም የግል ጫት ላኪ የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ካላከበረ ወይም በማንኛውም ሁኔታ የጫት ወጪ ንግድ ሥራን ካደናቀፈ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት አስፈላጊው ሕጋዊና አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰድበታል።

9. የሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነት

በዚህ መመሪያ ባልተካተቱ ጉዳዮች ላይ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 67/89 እና የፌዴራል መንግሥት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 13/89 ድንጋጌዎች እንደአግባቡ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

10. መመሪያውን ስለማሻሻል

ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል።

11. የተሻረ መመሪያ

በሚኒስቴሩ ሰኔ 14 ቀን 1993 ዓ.ም ፀንቶ የወጣው መመሪያ ቁጥር 4/1993 ተሽሮ በዚህ መመሪያ ተተክቷል።

12. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከሐምሌ 1 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም